# PANORAMA # XXXVIII

## የትዝብት  አድማስ

ነሀሴ 17 ቀን 20000

## የኢትዮጵያ ማንነትና  የውጭ ኃይሎች

ጥንታዊት ሀገር መሆኗ ብቻ ሳይሆን፥ ከአለችበት አህጉር ካሉ ሀገራት በእጅጉ የሚለይዋት በርካታ መሠረታዊ ባኅርይና ታሪክ ያላት በመሆኗም ጭምር፥ ሀገራችን በዘመናት የውጭ ኃይሎችን ቀልብ ስትስብ ኖራለች፡፡ ይህ መስኅብ አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡ ይህ መስህብ ደግሞ በአመዛኙ የደግነት ሳይሆን፥ የመጥፎነትና እንዲያውም አልፎ ተርፎ በውጭ ኃይሎች ዘንድ፥ በዐይነ-ቁራኛ እንደተታይ ሲያደርጋት ቆይቷል፡፡ በተደጋጋሚ የባዕድ ወራሪዎች ሰለባ ሲያደርጋትም ነበር ፡፡ በአፍሪካ አህጉር ብቸኛ ነፃ ሀገር ሆና በመቆየቷም፥ በቅኝ ግዛት ሲማቀቁ ለነበሩ የአህጉሩ ሕዝቦች የነፃነት ምልክት ስለነበረችም ይህ ስብዕናዋ ለምዕራባውያን ቅኝ ገዥዎች የጉሮሮ አጥንት ሆና ቆይቷል፡፡ የ“ጨለማው አህጉር” ሲባል ለነበረው አፍሪካም እንደ ብርሃን ፍንጣቂ፥ እንደ ነፃነት ውጋጋን ሆና ቆይታለች፡፡ ይህ ሁሉ ተዳምሮ ምዕራባውያን፥ ኢትዮጵያን በመዳፋቸው ውስጥ እንድትገባላቸው ያልሞከሩት ጥረት አልነበረም፡፡ ሙከራቸው ሁሉ እንዳልሆነ ሆኖባቸው፥ በጥንታዊው ጀግና ትውልድ መሥዋዕት፥ የቅኝ ግዛትን ውርደት ሳትቀምስ ለመቆየት ችላለች፡፡ ያ ጀግና ትውልድ ታዲያ፥ ኢትዮጵያን ብሔራዊ ውርደት የሚባል ሀፍረት እንዳይገጥማት አድርጓት ቆይቷል፡፡ የዛሬውን አያድርገውና! ለዚህም ይመስላል ይህ የዛሬው ትውልድ፥ “ ታርሶም ተሸምቶም ይበላል እንጀራ፥ ጥቃት ግን መረር ነው የሞት ባልንጀራ” እያለ የሚያጉረመርመው፡፡ ሀገሩ በወያኔ ስለተጠቃች፥ ስለተዋረደች ይህን ቢል ታዲያ የሚታዘንለት እንጅ የሚፈረድበት አልሆነም፡፡

ከ60ዎቹ ዓመታት በፊት አንድም የአፍሪካ ሀገር( ከላይቤርያና ከግብፅ በቀር) ነፃ ስለአልነበር፥ የኢትዮጵያ የውጭ ፖሊሲ ፥ “በቅኝ ግዛት ያሉ የአፍሪካ ሀገሮች ነፃነታቸውን እስካላገኙ ድረስ፥ ኢትዮጵያ ራሷን እንደነፃ ሀገር አትቆጥርም” በሚል መርኅ ዙሪያ የተቃኘ ነበር፡፡ ይህንንም የፖሊሲ ውሳኔ በተግባር ለመተርጎም የተቻላትን ሁሉ አድርጋለች፡፡ ለአፍሪካ ሀገራት፥ አቅሟ የፈቀደላትን ዕርዳታ ሁሉ ሰጥታለች፡፡ የደቡብ አፍሪካን የነፃነት ታጋዮች እነ ኔልሰን ማንዴላንም ጭምር--አሰልጥናለች፡፡ ሀገራቸው በቅኝ ገዦዎች ስር ያሉ ተማሪዎችን በነፃ አስተምራለች፡፡ በዚህም ሳቢያ፥ የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎች ሀገራችንን በሁለንተናዊ ተፅዕኗቸው ሲያጠቋት ቆይተዋል፡፡ የውስጥ ሠላምና ፀጥታ አግኝታ ወደ ልማትና ዕድገት እንዳታተኩር ሲያዉኳት ቆይተዋል፡፡ በአፍሪካ ቀንድ ጠንካራ ሀገር የሆነች ኢትዮጵያን ማየት ቀርቶ መስማት አይፈልጉም ነበር፡፡ ያ የቆየ ኅልማቸው ግን ዛሬ ዕውን በመሆኑ፥ መለስ

ዜናዊን አቅፈው ደግፈው ይዘውታል፡፡ በታሪካቸው እንደ መለስ ዜናዊ የመሰለ ታማኝ አገልጋይና ተንበርካኪ አሽከር ገጥሟቸው ስለማያውቅም፥ ወደ ፊትም እንደማይገጥማቸው በሚገባ ተረድተውታል፡፡ ለዚህ ተግባራቸው አስፈፃሚ መለስ ዜናዊ እንደሆነም አውቀውታል፡፡ የተከፋፈለች፥  የተቆራረሰች፥ ደካማና ድሀ ሀገር ሆና መቆየቷን በእጅጉ ይፈልጉታል፡፡  የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፥ ከዚህ ብሔራዊ ውርደት፥ ጥቃትና ጥፋት ለመዳን ያላት ምርጫ ያው አንድነትን አጠንክሮ ከመታገል የተሻለ ፍቱን መድኃኒት አይገኝም፡፡  የዛሬው ትውልድ ይህንን ማድረግ የሚገባው ከራሱ ኅልውና አንፃርም  ጭምር ነው፡ እራሱ ጠፍቶ የጠፋች ሀገር ለነገው ላላጠፋ ትውልድ ማስረከብ እንዴት እንደሚችል የሁሉም ሰው ጭንቀትና ጥበት ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ ለዘመናት፥ ኢትዮጵያ፥ ኢትዮጵያ ሆና በመገኘቷ ብቻ ብዙ ችግሮች እንደገጠሚት መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዘመናት የውጭ ጠላቶቿን እየተቋቋመች ኅልውናዋን ጠብቃ መቆየቷ ባይካድም፥ የዛሬውን የውስጥ ጠላቷን ግን መቋቋም ከማትችልበት ደረጃ ደርሳለች፡፡ የውጭና የውስጥ ጠላቶች ከተባባሩ ደግሞ፥ የአንድ ሀገር እንደ ሀገር  የመኖር ተስፋው የመነመነ  ይሆናል፡፡ ሕዝብ  አንድ አካል-አንድ አምሳል ሆኖ አብሮ ካልቆመ ፥ከተቃጣበት ጥፋት ለመዳን ይከብደዋልናም ነው፡፡

እረ ለመሆኑ  የኢትዮጵያን ዕጣ ፋንታ  ከሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች በተለየ ሁኔታ ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው? ይህንን ጥያቄ በአገባቡ  ለመመለስ የሚያስቸሉ በቂና አሳማኝ ምክንያቶች አሉ፡፡

ከሁሉ በፊት ኢትዮጵያ በመልከዐ- ምድር አቀማመጧ፥ የጂኦ ፖሊቲካ ጠቃሚ ነትና አስፈላጊነትን የተላበሰ ማዕከል ነች፡፡ በዚህ ስትራተጂያዊ ማዕከልነቷ በዘመናት የተፈራረቁት ኃያላን  መንግሥታት ለመቆጣጠር ተሻምተውባታል፡፡ ተፋልመውባታል፡፡ ተራኩተውባታል፡፡ የእነርሱ መራኮትም ሰለባ ሆና ቆይታለች፡፡  የአያሌ ዘመናት ያልተቋረጠ  የመንግሥት ሥርዓትና አስተዳደርና መዘርጋቷ፤ ለሌሎች የዓለም ጥቁር ሕዝቦች አርዓያ ሆና ቆይታለች፡፡ ዛሬ እነ መለስ ዜናዊ ብጣሽ ጨርቅ ነው ብለው ቢያረክሱትም፥ በጥንታዊነቱ የታወቀና የነፃነት ምልክቷ የሆነው ክቡር ሰንደቅ ዓላማዋ መውለብለቡ፥ ነፃነት ለጠማቸው የዓለም ጥቁር ሕዝቦች ሁሉ ሳይቀር፥ የነፃነታቸው ተስፋና ዓርማ ሆኖ ቆይቷል፡፡  የራሷ ፊደል ሥነጽሁፍ፥ ቅርፅ፥ የህንፃ ሥራዎች፥ ኃውልቶችና የታሪክ ቅርሶች የነበሯት በመሆኗ፥ ለአውሮፓ ሥልጣኔና ባኅል ሳታኅበድድ ቆይታለች፡፡ ነባርና ታላላቅ ሃይማኖቶችን በተፅዕኖ ሳይሆን፥ በሰላምና በበጎ ፈቀዷ  የተቀበለች ሀገር በመሆኗ፥ ምዕመናኑ በሌሎች ሀገራት እንደተከሰተው ችግር ሳይገጥማቸው በመተባባር የሚኖሩባት ነበረች/ናትም፡፡ እንደ ዛሬው ሳይሆን፥ ዜጎቿን በመመገብ በኩል እምብዛም ችግር አልነበረባትም ቢባል ከዕውነት የራቀ አይደለም፡፡ በታሪኳ፥ እንደዛሬው የውጭ ምፅዋዕት ጠይቃ አታውቅም  ነበር፡፡ ይህም በራስ የመተማመንና የአትንኩኝ- የአትድረሱብኝ ባኅርይ፥ ለቅኝ ገዥዎች ተኅብዳጅ እንዳትሆን ረድቷታል፡፡ ይህንን  የማንነት ኅላዊ ደግሞ፥ ቅኝ ገዥዎች አልወደዱላትም፡፡ ኢትዮጵያን አምበርክኮ- አሰግዶ ለመግዛት

እልህ እንዲያድርባቸው ምክንያት ሆኖላቸው ቆይቷል፡፡ እልህ የተጋቡትም፥ ኢትዮጵያን አንበርክኮ ለመግዛት ብቻ ሳይሆን፥ በቅኝ ግዛታቸው ስር የሚማቅቁት ሕዝቦች፥ የኢትዮጵያን አርዓያ በማየት ለነፃነታቸው ሲሉ፥ የአመፅ ትግል እንዳይጀምሩ በመፍራትም ጭምር ነበር፡፡ ለዚህም ነበር በአስራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ ላይ አፍሪካን ለመቀራመት ሲባል በበርሊን ከተማ የተሰበሰበው የአውሮፓ የቅኝ ገዥዎች ጉባዔ፥ በኢትዮጵያ ላይ የተለየ ጥላሸት በመጣል፥ የቅኝ ግዛት ዓላማቸውን ለማሳካት በአዲስ መልክ ሊንቀሳቀሱ የቻሉት፡፡ ጣሊያኖች፥ እንግሊዞች፥ የኦቶማን ኢምፓየር (ማለትም ቱርኮችና) ግብፆችም ሳይቀሩ ለማንበርከክ ተፈራርቀውባታል፡፡ ሁሉንም እንደ አመጣጣቸው እያሳፈረች መልሳቸዋለች፡፡ ይህ ዕቅዳቸው ሊሳካላቸው ባለመቻሉ፥ የውስጥ ብጥብጥ እንዲነሳ ለማድረግ የውስጥ ቅጥረኞችን መግዛትና ማሰልጠን ነበረባቸው፡፡ ዛሬም ይህን ሂደት በረቀቀ ዘዴ እያደረጉት ናቸው፡፡ በየዘመናቱ ዕርከኖች፥ ባዕዳን ምን ጊዜም ቢሆን፥ ኢትዮጵያ የጠነከረችና ኃያል ሀገር እንዳትሆን የሚፈልጉባት ዐቢይ ምክንያት፥አፍሪካን አህጉር ለመበዝበዝ በሚያደረጉት ጥረት ሁሉ እንደ እንቅፋት ስለሚቆጥሯት ነበር፡፡

በየካቲት ስድሳ ስድስቱ የፈነዳው የሕዝባዊ እንቅስቃሴ፥ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሶት የመነጨ፥ በኢትዮጵያ ሕዝብ የተካሄደና በባኅርዩም ይሁን በዓላማው ፍፁም ብሔራዊ የሆነ አብዮታዊ ነበር፡፡ እስከ ተወሰነ ሂደት ድረስ፡፡ ይህ ያልታሰበና ሀገር አቀፍ የሆነ የሕዝብ እንቅስቃሴ፥ ባዕዳንን ሁሉ ያስደነገጠና ያርበተበተም ነበር፡፡ ሕዝባዊና ስር ነቀል ባኅርይና አዝማሚያ ይዞ የተነሳ በመሆኑም፥ ፍራቻቸው ይበልጡኑ እንዲባባስ ሆኗል፡፡ ይህን ኢትዮጵያዊ አብዮት ለመቀልበስም ሆነ ለማኮላሸት፥ ብሎም በራሳቸው ቁጥጥር ለማስገባት ሁሉም ባዕዳን ኃይሎች በኢትዮጵያ ላይ ተረባርበዋል፡፡ በዘመናት የኢትዮጵያን ሀገራዊ እንቅስቃሴ ለማክሰም የቱን ያኅል እንደጣሩ ሦስት ማስረጃዎች ለመጥ ቀስ ብንሞክር ሁኔታውን በይበልጥ ግልፅ ያደርገዋል ብለን እንገምታለን፡፡

ሀ) በዘመነ ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ፥ ማለት በ19ኛው አጋማሽ አፍሪካን ለመቀራመት በተደረገው ሴራ፤ ኢትዮጵያን፥ የወረራቸው ዕቅድ ግምባር ቀደም ዒላማ አድርገዋት ነበር፡፡ ለዚህም ሰበብ ያደረጉት ለአፍሪካ ቅኝ ግዛቶቻቸው የነፃነት ምልክትና የፀረ ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ ተምሰሌት ትሆንብናለች ብለው ስለአመኑ ነበር፡፡ በተለይ በ1888 ዓ.ም የኢጣልያንን ወረራ አድዋ ላይ በአሸናፊነት በማክሸፏ ምዕራብያውያን ቅኝ ገዥዎችይበልጡኑ ፍራቻቸውና ጥላቻቸው ጨመረ፡፡ እንደምን ብለው ኢትዮጵያን የቅኝ ግዛት መዳፋቸው ሰለባ ካልሆነች፥ ጤና እንደምትነሳቸው አረጋገጡ፡፡ይህንም ከአርባ ዓመት በኋላ በ1928 ዓ.ም በዳግመኛ ወረራቸው አረጋግጠዋል፡፡ ከአምስት ዓመታት የአርበኞች ቆራጥ ተጋድሎ በኋላ የአድዋው ድል እስከተደገመ ድረስ፥ ኢትዮጵያን በመዳፋቸው ለማስገባት፥ ጥረታቸውን አላቋረጡም ነበር፡፡

ለ) የአፍሪካ አህጉር ብቸኛዋ ነፃ ሀገር በመሆኗም፥ ከቅኝ ግዛት ነፃ

ለመውጣት የሚዋጉትንም የአፍሪካ ሀገሮች በመርዳቷ፥ የቅኝ ገዥዎች የግልፅና የድብቅ ሴራ ጥቃት ደርሶባታል፡፡ ኢትዮጵያን አጥፍተን ካላጠፋናት ቅኝ ግዛቶቻችን ጠቅላላ የነፃነት አመፅ መቀጠላቸውን አያቆሙም ብለው በመደምደማቸው፥በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ በመግባት የውስጥ ቅጥረኞቻቸውን በማሰልጠንና ተገንጣዮችንም በመርዳት ሲጎዷት ኖረዋል፡፡ ሰላም ነስተው በድኅነትና በብጥብጥ እንድትማስንም አድርገዋል፡፡የቅርብም የሩቁም ጠላቶች እነ ወያኔንም የዕቅዳቸው አስፈፃሚ አድርገዋቸዋል፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ ተጨማሪ ምዕራፍ መሄድ የሚገባን አይመስለንም፡፡ ሌላው ታሪክ ነውና፡፡

ሐ) የስድሳ ስድስቱን የኢትዮጵያ ዐብዮት ወደሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ተዛምቶ አህጉሩን ከማጥለቅለቁ በፊት ለማኮለሽት፥ በተራቀቀ ሴራች ተጠቅመው፤ ያሰቡትን አድርገዋል፡፡ ይህንን የተሳካ ውጤት ሊያስመዘግቡ የበቁት፥ ለዚህ ተግባራቸው የሚጠቅሟቸውን ሰላዮቻቸውን ለብዙ ጊዜ አስልጥነውና በኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ተቋማት ሰርስረው እንዲገቡ በማድረግ ነበር፡፡ ይህ ብሔራዊ ባለቤትና ተቆርቋሪ ያልነበረው ዐብዮት፥ተኮላሽቶ እንዲቀርና ከፍተኛ ጥፋት እንዲያስከትል የተደረገው፥ በውጭ ሰላዮች በተመለመሉ ምሁራንና በሙያተኞች ነበር፡፡ የመጀመሪያው የጥፋቱ ሰለባና ዒላማ የሆኑት፥ ሀገር ወዳድ ምሁራን፥ ከአምሳዎቹ ዓመታት ጀምሮ ለውጥ እንዲመጣ ሲታገል የነበረው ተራማጅ ትውልድ፥ እንዲሁም ሀገራቸውን ከልዩ ልዩ የውጭ ጠላቶች በመከላከል ከፍተኛ መሥዋዕት የከፈሉ አርበኞችና የሃይማኖት መሪዎች ነበሩ፡፡ እነኝህ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተለይ የግምባር ቀደም ዒላማና የጥፋቱ ሰለባ ሊሆኑ የበቁት፥በሀገራቸው ነፃነትና ልዕልና፥ በሕዝባቸውም ፍቅር ቀናዒ በመሆናቸው ብቻ ነበር፡፡ ባዕዳኑ፥ የኢትዮጵያ ዐብዮት ከተሳካ፥ ኢትዮጵያ የጠነከረች፥ የበለፀገችና ምናልባትም፥በአፍሪካ አህጉር ተወዳዳሪ የሌላት ተራማጇ ሀገር ትሆናለች ብለው በመገመታቸው፥ ስለ ዐብዮቱም ሆነ ስለ ሕዝብ ፍቅር ምንም ዝግጅትና ዕውቀት የሌለውን ደርግ በቅጥረኞቻቸው ምሁራን አማካኝነት ሥልጣን እንዲይዝ አደረጉት፡፡ የመኮንኖቹም ቡድን ዐብዮቱን አኮላሽቶ፥ ዕልፍ አዕላፍ ሕዝብ ጨርሶ፥ ሀገር አጥፍቶ፥ አውቆትም ይሁን ሳያውቀው፥ የውጭ ባዕዳንን የቆየ ዕቅድ ፈፅሞላቸው እርሱም ተንኖ ቀረ፡፡ ይህን አገዛዝ የተካውም መለስ ዜናዊ፥ የኢትዮጵያን የመጨረሻ ግብዓ-ተመሬት ለማከናወን የምዕራብያውያንን የመጨረሻ ዓለማ ለመፈፀም ተግቶ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

በዕኛ ዕምነት፥ የባዕዳን ኢትዮጵያን የመከታተልና እስከ መጨረሻው የማጥፋት ዘመቻ በወያኔ መወገድ ምክንያት ያበቃል ለማለት ይከብዳል፡፡ በዝባዥ ባዕዶች አፍሪካን አዳክመው መግዛት መቆጣጠር ይፍልጋሉ፡፡ ስለዚህም አንድ ኢትዮጵያ፤ናይጀሪያ፤ ኮንጎ፤ ደቡብ አፍሪካ ዓይነቶቹን ታላላቅ ሀገሮች ማንበርከክና መከፋፋል ይመኛሉ፡፡ በመሆኑም ለነገዋ ኢትዮጵያ የጥፋት ድግስ እየተጠነሰሰ እንደሆነ ልንክደው አንችልም፡፡

አሁንም ተቃዋሚ ኃይሎችን በተራቀቀ መንገድ መከፋፈሉ ቀጥሏል፡፡ ተቃዋሚዎቹ ጠንክረው ወያኔን አስወግደው ሀገራቸውን ከጥፋት እንዳያድኑ፥ ምዕራባውያን፥ የነገ አገልጋዮቻቸውን እያዘጋጁ እንደሆነ ለመላው ኢትዮጵያ በሚገባ ግልፅ ሆኖለታል፡፡ በመሆኑም ዛሬ ይህንን አደጋ በሚመለከት መላው ሕዝባችን ያለው ምርጫ፥ አንድ ብቻ ነው፡፡ የየድርጅቶችን ዓላማና ግብ፤ ባኅርይና ተግባር፥ ብሎም ማን የባዕድ አሽከር እንደሆነ ? ማንስ ለሀገሩና ለሕዝቡ ጥቅም እንደቆመ ለይቶ ማወቅና ሀገርን ለመጠበቅ ነቅቶ መታገል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ማንነት ዛሬም እንደ ጥንቱ ለባዕዳን እንደማይመቻቸው በሚገባ ያውቁታል፡፡ የኢትዮጵያን የመጨረሻ ጥፋት ካላዩ እንደማይተኙ በማወቅ፥ ኢትዮጵያዊው ሁሉ በመተባበር ሀገሩን ከጥፋት ማዳን የያንዳንዱ ዜጋ ሀገራዊ ኃላፊነትና የወቅቱ አንገብጋቢ ጥሪ መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል፡፡ ሀገራችንን ከጥፋት ለማዳንም በራሳችን ላይ መተማመን እንጂ ባበዕዳን ላይ መቸም ቢሆን መመካት የለብንም፡፡ መለስ ብለን ታሪካችንን ብንመረምር ኢትዮጵያን ከጥፋት ያዳኗት ጅግኖቹ ልጆቿ እንጂ ባዕዳን ሆነው አያውቁም፡፡ ዛሬም ሌላ ሀቅ የለም፤ ነገም አይኖርም፡፡